ዴሞክራሲያ

* የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ልሳን *

ዴሞ ቅጽ 44 ቁ. 2 ጥቅምት/ኅዳር 2011

## አለባብሰው ቢያርሱ በአረም ይመለሱ !

ዛሬ በሀገራችን፣ ወደ ኋላ ሊቀለበስ የማይችል በሕዝብ አመጽ የሚካሄድ ለውጥ አለ። የለውጡ መዳረሻ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ኢንዲሆን ሁሉም ዜጋ ጓንቶ ይጠብቃል። እንደሚሳከም ያምንበታል። የለውጡ አቅጣጫና አካሄድ ምን ሳንካ ያጋጥመው ይሆን በማለት በሥጋትና በተመስጦ የሚከታተሉ አያሌ ወገኖች አሉ። የመጀመሪያው ባለጉዳይ ለውጡን በትግሉ ያስገኘው፤ አመፀኛው ያው ራሱ የኢትዮጵያ ሕዝብ ለመሆኑ አጠራጣሪ አይሆንም። ለውጡ ሳንካ ገጥሞት ተንገራግጮ እንዲሰናከል የማይፈልገው ሕዝብ፤ ላስገኘው ለውጥ ቀናዒ ነው። ሁለተኛው ለአለፉት ሃያ ሰባት ዓመታት የኢትዮጵያን ሕዝብ ጨቁኖ በመግዛት ሀብቷን ሲመዘብርና ንብረቷን ሲያሸሽ የነበረው ወያኔና ተባባሪው ክፍል ደግሞ የነበረውን ጥቅም ለማቆየት ሲል ለውጡ እንዲሰናከልለት ይመኛል። በሦስተኛ ደረጃ፡ ኢትዮጵያን ከዕይታው ጨርሶ ሊያወጣት የማይፈለገው የውጭ ኃይል ነው። የውጭው ባዕድ ኃይል፣ በሀገሪቱ ላይ ሥልጣን የሚይዘውን ማንኛውንም መንግሥት፤ በሆነው ዘዴ የመቆጣጠር ኃይል እስካላገኘ ድረስ፤ ተንኮል ከመሸረብ ፈፅሞ አይተኛም። ለዚህም ቅጥረኞች አያጣም።

የትግሉ ተቃርኖ የከረረው ግን ፤ ነፃነቱንና መብቱን ለማስከበር ዐመፅ በሚያካሂደው ሕዝብና ለውጡን ለመቀልበስ በሚቅለበለበው በወያኔ መካከል ነው። የመጨረሻው አቸናፊ የሚሆነው ሕዝባዊው ዐመፅ መሆኑ የታሪክ ዕውነታ ስለሆነ፤ የለውጡ አደናቃፊዎች ጥረት መና ሆኖ ይቀራል። ያ ስለተባለ ግን የሚካሄደው ለውጥ፤ ከሳንካ ነፃ ነው ፤ ሁሉ ነገር አልጋ ባልጋ ነው ማለት አይደለም።

የተጀመረው ሕዝባዊ ዐመፅ፤ ሀገሪቱን ዘላቂ ወደሆነ ሠላማዊ መረጋጋት እንዲያሸጋግራት ከተፈለገ፤ የሥርዓት ለውጥ ማምጣት፤ ፍቱን መድኃኒት መሆኑ ተፈጥሯዊ ነው። በዘረኛ አምባገነን ላይ ከተገነባ አገዛዝ፤ ወደ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ለመምጣት፤ በመሃሉ የግድ የሽግግር ወቅት አስፈላጊ እንደነበር ቀደም ባለው የፖለቲካ ታሪኳ፤ ሀገራችን በቁጭትና በፀፀት የምታስታውሰው ጠባሳ ሆኖባት አልፏል።

የስድሳ ስድስቱ ሕዝባዊ ዐመፅ በሠላማዊ የሽግግር ሂደት አልፎ ቢሆን ኖሮ፤ ሀገሪቱን ላለፉት ግማሽ ምዕተ-ዐመት ከገጠማት ምስቅልቅል ትተርፍ ነበር ተብሎ ይታምናል። ያ ሳይሆን ቀርቶ፤ ከነበረው እጅግ ኋላ-ቀር መሳፍንታዊ አምባገነን አገዛዝ፤ ያለ ምንም ዝግጅትና የመሸጋገሪያ ወቅት፤ ወደ ባሰ ወታደራዊና ፋሽስታዊ አምባገነን አገዛዝ ተለወጠ። ኅብረተሰቡም፤ ካንድ ፅንፍ ሥርዓት-አገዛዝ ለሌላኛው ፅንፍ ሥርዓተ አገዛዝ ተዳረገ።

ያለምንም ዝግጅትና ማስተዋል፤ በችኮላ የተገነባው ሥርዓተ-አጋዛዝ፤ የሽግግር ወቅትን ሂደት ባለማለፉ ምክንያት፣ እርሱ ደንብሮ፤ አጫፋሪዎቹንም አደናብሮ ፤ ሀገሪቱንም ምስቅልቅል ውስጥ አስግብቶ፤ እንደ ነሐሴ ጉም በንኖ ጠፋ። የአሁኑ የሀገራችን አስጊ ሁኔታ፤ የደርግና የወያኔ ድምር ወጤት ነው ቢባል ስህተት አይሆንም። የሁለቱ ዓላማ ግን የተለያየ ነበር።

ወታደሮቹ ኢትዮጵያ ትቅደም ብለው ተነሱና ኢትዮጵያን አጥፈተው ጠፉ። ወያኔ ደግሞ፤ ትግራይን ለማስገንጠል ተነሳና መላ ሀገራችንን እያጠፋት ይገኛል። ወያኔ ለትግራይም፣ ለኢትዮጵያም፣ ለራሱም ሳይሆን ከረመ። ባሁኑ ወቅት፣ ከተነሳበት ዋሻ ውስጥ ገብቶ አድፍጦ ይቁለጨለጫል። በትንሣዔ ኢትዮጵያን ምህረት ከጠየቀ፤ መሃሪዋ ኢትዮጵያ ይቅርታዋን አትነፍገውም። ለንሰሀ መዘጋጀት ግን ይኖርበታል። የተጀመረውን ለውጥ ለማደናቀፍ መፍጨርጨር ደግሞ ከተመክሮ ለመገንዘብ እንደሚቻለው የራስ መጥፊያ እንጅ እርባና የለውም። እንዲያውም፤ ሠላም መስፈኑ እየቀረ፤ ሁከትና ብጥብጥ ይተካል። ዛሬ ሀገሪቱ ያለችበት ሁኔታም ወደዚያ የሚያመራ ሽታ የሰፈነባት ሆናለች።

አሁን በሥልጣን ላይ የሚገኘው ቡድን፤ አደገኛ አቅጣጫውን ሳይገነዘበው ቀርቷል ማለት አይቻልም። በመፍትሄው ፍለጋ ላይ የቱን ያህል እንደተጨነቀበት እንደሆነ ግን ራሱ ብቻ ነው ሊያውቀው የሚችለው። ብቻውን ደግሞ መፍትሄ ሊያመጣ አይችልም። የህዝብ ሙሉ ተሳትፎ ወሳኝ ነውና ሕዝቡን ማሳተፍ የቅድሚያ ቅድሚያ ሆኖ ሊሠራበት ይገባል። የሕዝብን ሙሉ ተሳትፎ ያላገኘ ለውጥ ተንገራግጮ የመቅረት ዕድሉ እጅግ የሰፋ ነው። በተቋማት ያልተደገፈ ህዝባዊ ዐመፅና የሚከተለው ለውጥም እንዲሁ ዋስትና የለውም።

ታሪክ በሌላ ወቅትና አጋጣሚ ራሱን ይደግማል የሚባል ከሆነ፤ ሀገራችን አሁን የገጠማት ታሪካዊ ሂደት፤ ከስድሳ ስድስቱ ዓ.ም የካቲት ዐመፅ የሽግግር ወቅት ጥያቄ አስፈላጊነት ጋር በመሠረታዊ መልኩ፤ ተዛማጅ ነው ማለት ያስችላል። ዛሬ ሀገራችን፣ ካንድ አክራሪ ጽንፋኛና ዘረኛ አገዛዝ ወደ ዴሞክራሲ ሥርዓተ-መንግሥት ለመሸጋገር በለውጥ ሂደት ላይ ትገኛለች። እንደ ስድሳ ስድስቱ ዓ.ም የካቲት ዐብዮት፤ ሀገር አቀፍ ጥያቄዎችን ያነገበ ሳይሆን፤ ብሔር ተኮር ዕይታን የናኘ ነው። ያንድነት ኃይሉ በጠንካራ አቋም ላይ ነው ማለት የሚቻል አይደለም። ከኅብረ ብሔር ድርጅቶች ይልቅ፤ የብሔር ድርጅቶች ቁጥርና እንቅስቃሴ የፖለቲካ አውታሩን አስፋፍቷል። ለአንድነት ግንዛቤ ቅድሚያና ትኩረት የማይሰጥ ድባብ ሰፍኗል - ለ27 ዓመታት በወያኔ አገዛዝ የተሠራውም ይህ እንዲሆን ነበረና! ብሔር-ተኮር እንቅስቃሴና ሀገር አቀፍ ትግል በሚዛን ካልተስተናገዱ ፤ የኢትዮጵያ ሀገራዊ አንድነት ዋስትና ማግኘቱ አጠራጣሪ ይሆናል።

ከዚህም በቀር፤ በብሔር ድርጅቶችና በኅብረ ብሔር ድርጅቶች መካከል ፤ በኢትዮጵያ የወደፊት ዕድል ላይ ተቀራራቢ ዕይታ ያለ መሆኑን በዕርግጠኝነት መናገር ከማይቻልበት ወቅት ተደርሷል። ሌላው አስደማሚ ጉዳይ፤ በራሳቸው በብሔር ድርጅቶች መካከልም እንኳ ቢሆን፤ ኢትዮጵያን በሚመለከት ተቀራራቢ ዕይታና አረዳድ ይኑራቸው አይኑራቸው የሚያጠያይቅ ሆኖ ይታያል።

የፖለቲካ አተያይ የሚመነዘረው ከኃይል ሚዛን አሰላለፍ አኳያ ነው እስከተባለ ድረስ፤ በሀገሪቱ የፖለቲካ መልከዐ ምድር፤ ዛሬ የኃይል ሚዛኑ ወዴት እንደሚያደላ፤ የፖለቲካ ኃይላቱ አሰላለፍ ምን እንደሚመስልና የኃይል ሚዛኑ በምን ደረጃ እንደሚገመገም በትክክል ለማወቅ ባልተቻለበት ሁኔታ፤ የሀገሪቱ የወደፊት አቅጣጫ ወዴት እንደሚያመራም ከምናልባታዊ ግምት በስተቀር፤ አፍን ሞልቶ ይህ ነው ብሎ መናገር የሚቻል አይመስልም።

የሕዝብን መሠረታዊ ጥያቄዎች በአግባቡ እየመለሱ ለውጡን ተንከባክቦ ይዞ ዓላማውን ለማስቀጠል የሚቻለው፤ ሁሉንም ባለድርሻዎች የሚያሳትፍ ሀገራዊ ፖሊሲ ነድፎ፤ በተግባር መተርጎም ሲቻል ነው የሚል የፀና እምነት አለን። ይኽ ሁኔታ ግን ዛሬ በሀገራችን ተግባራዊ ሁኖ ሰፍኗል ማለት አይቻልም። በፖለቲካ ሂደት፤ በጎ ፈቃድና ምኞት ብቻውን ካሰቡት ግብ አያደርስም። የወጡትን ፖሊሲዎች በተግባር ለመተርጎም ተጨባጭ እንቅስቃሴዎች ካልተደረጉ በስተቀር፤ የሀገር መረጋጋትና የሕዝብ ሠላም ማግኘት ያስቸግራል። ይህንን አባባል አሁን ያለው የሀገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታ እያረጋገጠው ይገኛል።
ሕዝቡ ካሳለፋቸው መራራ ችግሮች በመነሳት፤ ለለውጡ ያለውን ድጋፍ፤ ያለ ተአቅቦ ቢቀጥልም፤ ሙሉ ተሳትፎ የሚያደርግበት ሁኔታና ዕድል አልተመቻቸለትም። የፖለቲካ ተውኔት የህዝብን ሙሉ ተሳትፎ ካላገኘ ፤ በአንድ እጅ ከማጨብጨብ ያለፈ ድምቀት አያገኝም። ሕዝብ በመስዋዕቱ ያስገኘውን ለውጥ ማንም ኃይል በብቸኝነት ሊቆጣጠረው መፍቀድ እንደገና መልሶ ወደ ጭቆና አዘቅት መግባት ይሆናል።

በመሆኑም ሕዝቡና ለሱ ቀናኢ የሆኑ ኃይላት በሙሉ የተስፋን ጮራ እንጅ፤ የፅልመት መስኮት እንዲከፈትባቸው የሚፈልጉ እንዳልሆኑ ደግሞ በሚያደርጉት እንቅስቃሴያቸው እያረጋገጡ ይገኛሉ።

ለሰላሙና ለደህንነቱ፤ ለሙብቱ መከበር አጥብቆ የሚጓጓው ሕዝብ፣ ሌላው ቀርቶ ወደ ዴሞክራሲያዊ ሂደት የሚያሸጋግርውን አቅጣጫ እንኳን ለማየት ጭላንጭሉ ደብዝዞበታል። ስለሆነም ከሞላ ጎደል፤ የሁሉንም ባለድርሻ ጥቅም ባካተተ መልኩ የሚያሳትፍ እርምጃ ቅድሚያ ሊሰጠው የግድ ይላል። ለዚህም ተስማሚና ተገቢ ወቅት፤ የሽግግር ሂደት ነው። ሥልጣን የጨበጠውን ኃይልም ሆነ፤ የኅብረተሰቡን ልዩ ልዩ ፍላጎቶች የሚወክሉና ሁሉንም የፖለቲካ ድርጅቶችን የሚያካትት የሽግግር ሂደት የሚያስፈለገውም ዋናው ዓላማ፤ ሠላምና መረጋጋት ለማስገኘቱ ብቻ ሳይሆን፤ የሀገሪቱን የወደፊት አቅጣጫ ለመቀየስ የሚያስችል መሠረት ለመጣልም ጭምር ነው። ያለ ጠንካራ መሠረት፤ አስተማማኝና ዘላቂ ሠላም የሚያመጣ የፖለቲካ ምኅዳር መፍጠር የሚቻል አይሆንም። ከእንግዲህ ወዲህ ሀገራችን፤ ከአንድ ዐይነት ብጥብጥ ወደ ሌላ ዐይነት ብጥብጥ ልትሸጋገር አይገባትም። ያለፈው ፍዳና ሰቆቃ ይበቃታል !

ወቅታዊው የሀገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታ በትክክል የሚያመለክተው፤ በተለያዩ ክፍሎች የእርስ በርስ ፍጅቶች፤ ግድያዎች፤ መፈናቀሎች ሀብት ንብረት ዝርፊያዎችና ሁከቶች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተበራከቱ መሄዳቸው ብቻ ሳይሆን፤ ከቁጥጥርም ውጭ እየሆኑ መምጣታቸውም ጭምር ነው። ኢትዮጵያ ዛሬም እንደትላንቱ ፤ ሠላም፣ ፀጥታና መረጋጋት የሚናፈቅባት ሀገር እየሆነች ነው። በሁሉም የሀገሪቱ ክፍል ህጻናትና አረጋውያን በሠላም ወጥተው በሠላም ወደ ቤታቸው የሚገቡባት ሀገር ነች ብሎ መናገር ከባድ እየከበደ ነው። በሀገር የቆዩት ታጣቂዎች ብቻ ሳይሆኑ፤ ከውጭ ሀገር የሚገቡት ኃይላት ሳይቀሩ ትጥቃቸውን አንፈታም ብለው የገዥውን ቡድን ኃይልና ሥልጣን እየተፈታተኑት የሚገኙባት ሀገር ሆናለች። ይህን ማድረጋቸው፤ የተማመኑባት ሌላ የወጭ ኃይል እንዳላቸው ይጠረጠራል።

በአንድ ሉዓላዊ ሀገር መሣሪያ ይዞ መንቀሳቀስ የሚችለው፤ ሕጋዊነቱ ያልታወቀ ሌላ ታጣቂ ኃይል ሳይሆን፤ በሕጋዊ መንግሥት ቁጥጥር ስር ሆኖ፤ በበላይ አለቆቹ ትዕዛዝ የሚንቀሳቀስ የሀገር መከላካያ ሠራዊት ብቻ ነው። ከዚህ ውጭ ሌላ ታጣቂ ኃይል ሊኖር አይችልም። ያ ካለ ግን፤ በመንግሥት ውስጥ መንግሥት፤ በሠራዊት ውስጥ ሠራዊት፤ እንዳለ ይቆጠራል። የወቅቱ የሀገራችን ሁኔታ አስጊ ደረጃ የደረሰውም ይህ ክስተት ስለሚታይ ነው። ይህ አገዛዝ፤ ራሱ ያወጣውን ሕግ ራሱ አክብሮ ማስከበር እንኳ አልሆነለትም።

ባለፈው ሣምንት፤ አንድ ሙሉ ሻለቃ የታጠቀ የመከላከያ ሠራዊት ከነትጥቁ በአስደንጋጭ ሁኔታ ወደ ቤተ መንግሥት በመግባት፤ በወያኔ የተሾመውን ጠቅላይ ሚንስትር ፤ ኮት አስወልቆ ጅምናስቲክ እያሰራ፤ ተኛ-ተነስ -ፑሽ -አፕ እንዲያሳይ አድርጎታል። ይህ ክስተት፤ ላየውም ለሰማውም አግራሞትን ፈጥሯል። ይህ የወታደሮች ሀገ-ወጥ ድርጊት መላውን ሕዝብ አስደምሟል። ነገ ምን እንደሚያስከትልም አሳስቦታል። ሕግና ሥነሥርዓት፤ አዛዥና ታዛዥ፤ ወታደራዊ ዲስፕሊንም ሆነ ፤ የትዕዛዝ ሰንሰለትና ጠገጉን ያልጠበቀ መከላካያ ሠራዊት፤ እንዴት አድርጎ ነው የዓለቆችን ትዕዛዝ አክብሮ፤ የሀገር መከላካያ ነው ሊባል የሚችለው? የውጭ ወራሪ ኃይልን በምን ተዐምር ነው መመከት የሚችለው? የሚል ጥያቄና ስጋት አስንስቷል። ከዚህም ባሻገር፤ ሀገሪቱን የሚመራው መንግሥት ተቀባይነቱን/ቅቡለነቱን፣ ሕጋዊነቱንና ኀልውናውን አጠራጣሪ አድርጎታል ቢባል የሚያስገርም የማይሆነውም ለዚህ ነው።
ይኸንን ተከትሎ ደግሞ፤ ሌሎች መሠረታዊ ጥያቄዎችን የሚጭሩ ሁኔታዎች ተፈጥረዋል። እነርሱም፣ አሁን በሥልጣን ላይ ያለውን የወያኔን ሹመኛ፤ ሦስት ተግዳሮቶች የሚፈታተኑት መሆናቸው ነው። የነርሱ መከሰት ደግሞ ለብዙ ጊዜ ታፍኖ የነበረው ኅብረተሰብ ዐመፅ ያመጣው ለውጥ ነው።

እነኝህ በኀባንነት የሚተያዩትና የሚፎካከሩት ባላንጣዎች፤ ለየራሳቸው ዐላማ ማስፈፀሚያ ስኬት ፍለጋ ይሯሯጣሉ።

በመጀመሪያው ረድፍ የሚገኘው አዲሱ ሹም ዐብይ አህመድ ሆኖ፤ የሕዝቡ መሠረታዊ ሥር-ነቀል ለውጥ እንዳይሳካ፤ የአፍዛዥ -አደንዛዥ ክኒን እያደለ ይገኛል፡፡ የሕዝቡን መሠረታዊና ዴሞክራሲያዊ ጥያቄዎችን

ለመቆጣጠር ይፈልጋል። በዚህ ምክንያት አወቀውም አላወቀውም ከሕዝቡ ጋር ቀስ በቀስ፤ ቅራኔ ውስጥ እየገባ መሄዱን ያሳያል። የጫጉላው ወራት እያለፈበት በመሄድ ላይ ነው እያሰኘ ነው። ከሕዝቡ ጋር አንድ አካል- አንድ አምሳል ሆኖ፤ የሕዝቡን መሠረታዊ ዴሞክራሲያዊ ጥያቄዎችን ማስተናገድ ሲገባው፤ የለውጡን ቅደም -ተከተል የሚያፋልስ ፖለቲካ ያራምዳል። የሁለት ተቃርኖ አመለካከቶች ሰለባ ሆኗል።

እነርሱም፤ በአንድ በኩል የወያኔን ኩርፊያ ለማስታመም የሚያደርገው ጥረት ሲሆን፤ በሌላ በኩል ደግሞ ከሞላ-ጎደል፤ የህዝቡን ጥያቄ ለማስተናገድ የሚያደርገው የፈራ ተባ ሙከራ ነው። አንድ ሎሌ ሁለቱን ጌቶች በእኩልነት ማስተናገድ ስለማይሆንለት፤ አንዱን መምረጥ የግድ ይላል። በመሠረቱ፤ በዘላቂነት የኢትዮጵያ ሕዝብ ወዳጅነት ተፈጥሯዊ በመሆኑ ዐብይ አህመድ ፤ ለኢትዮጵያና ለዜጎቿ ስትራተጂያዊ ጥቅም መቆም አለበት። ምርጫው ግን የራሱ ስለሆነ፤ ጨው ለራሱ ሲል መጣፈጥ አለበትና ድንጋይ ተብሎ እንዳይጣል፤ ሊያስብበት ይገባል።

ሁለተኛዎቹ ተግዳሮቶች፤ የቆየ ዐላማቸውን ለማሳካት ምቹ አጋጣሚ መጥቶልናል ብለው የሚያስቡ አንዳንድ ብሔረተኛ ድርጅቶች ናቸው። አሁን የመጣውን ለውጥ ለራሳቸው ዓላማ ብቻ ማስፈፀሚያ ለማመቻቸት፤ ዐብይ አህመድን እየደገፉ መቃወም፤ እየተቃወሙ መደገፍ በሚል ዘዴ ይጓዛሉ። ፍላጎታቸው፤ በሕዝብ መሥዋዕት የተገኘውን ለውጥ ሙሉ በሙሉ ለራሳቸው ዐላማ ማስፈፀሚያ በማድረግ፤ የመጨረሻ ግባቸውን መምታት ነው። ለውጡን ከራሳቸው ጠባብ ጥቅም ማስጠበቂያ አንፃር እንጅ፤ ከመላው ህዝብና ከሀገሪቱ ዘላቂ ጥቅም አኳያ ሊያዩት የሚፈልጉ አይመስሉም። ለሁሉም ዜጋ እኩል ተጠቃሚ ልትሆን የምትችለውን ኢትዮጵያ ከመገንባት ይልቅ፤ የቅድሚያ አጀንዳ አድርገው የሚንቀሳቀሱት፤ ለራሳቸው ጠባብ ጥቅም ነው። ሌላው ዜጋ፣ ኢትዮጵያ ሁሉም ህዝቧ በጋራ የሚጠቀምባት ሀገር እንድትሆን ነው ተግቶ የሚሰራው። የተለየ አማራጭ እንደሌለ ፤ የሀገሩን ኅልውና አጥብቆ የሚፈልግ ዜጋ ሁሉ ዕምነትና ፍላጎት እንደሆነ ማንም አይስተውም። ዛሬ ሀገራችን፤ ከምንም በላይ በሀገራዊ ጥቅሟ የማይደራደር መሪ ያስፈልጋታል።

በሦስተኛ ደረጃ ፤ ይህ ለውጥ ያነጣጠረው በእኔ ጥቅምና ህልውና ላይ ነው ብሎ የሚያስበው ወያኔ ነው። የመጣውን ለውጥ ለመቀልበስና የተነጠቀውን ሥልጣን ለማስመለስ አድፍጦ ማወኩን ይቀጥላል። ይኸ ምኞቱ ከተሳካለት ተሳካለት፤ ካልተሳከላት ደግሞ፤ የትግራይን መሬት የመጀመሪያ መከላከያ መስመሩ አድርጎ፤ እስከተወሰነ ጊዜ ኅልውናውን ለማቆየት ይጥራል። የመከላከያ ምሽግ በመቆፈር ላይ እንደሆነም ተያያዥ አመላካች መረጃዎች በመከሰት ላይ ናቸው። የወያኔን ዕኩይ ተግባር፤ መላው የትግራይ ህዝብ ይጋራዋል፤ ያስተናግደዋል ማለት ግን አይደለም ።

በነዚህ ተግዳሮቶች ውስጥ ተዋናዩ በመራራ ትግሉ ያገኘው ለውጥ ግቡን እንዲመታለት የሚፈልገው ያው፤ መላው አሳረኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው። የተለየዩ እንቅፋቶች ቢጋረጡበትም፤ በትግሉ ያገኘውን ለውጥ ላለማስቀልበስ፤ ተግቶ ይከላከላል። ብርቱ መሥዋዕት የሚያስከፍል ትግል እንደሚጠብቀውም ይረዳል። ከባርነት ይልቅ ነፃነትን መርጦ ቆርጦ ስለተነሳ፤ አሽቀንጥሮ ወደ ጣለው ወደ ወያኔ ዘረኛ አገዛዝ ተመልሶ የመሄድ ፍላጎቱም አምሮትም የለውም። ይልቁንም፤ በተቻለው መጠን፤ ኃይሉን አስተባብሮ ፤ ትግሉን እስከ መጨራሻው ግብ ለማድረስ ዐመፁን ይቀጥላል። ኢሕአፓም እንደተለመደው፤ ከሕዝብ ጎን ቆሞ ትግሉን ያካሄዳል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ አሁን በሥልጣን ላይ ለሚገኘው ቡድን አንፃራዊ የሆነ፤ ነገር ግን፤ የአስተውሎ ድጋፍ የሚሳየውም፤ የራሱ ዕሳቤ እንዳለው ይገመታል ። ይህ እንዳለ ቢመስልም፤ በሌላ አኳያ ደግሞ በሕዝቡ አንፃራዊም ሆነ ለዘብተኛ ድጋፍና በአገዛዙ አራማጆች መካከል የተገኘ ነፃ ተቋም ባለመኖሩ፤ ለውጡ በአስተማማኝ አኳኋን፤ ያለ መሰናክል ይቀጥላል ብሎ አፍን ሞልቶ ለመግለፅ ያስቸግራል። ሕዝቡ ይህንን ስጋት እንዲያውጠነጥን የሚያስችሉ ከምናልባታዊ አመለካከት የመነጩ ምክንያቶች ተደንቅረውበታል። የወቅቱም ሁኔታ ምን ሊገጥመው እንደሚችል፤ በሦስት ኮነቶች ሊገለፁ ይችላሉ።

1ኛው. ሠላምም ሆነ መረጋጋት፣ መተማመንም ሆነ ቁርጠኝነት ባልሰከነበት አኳኋን፤ ሀገሪቱ በጅዋ ጅዌ መንገድ ወደምትቀጥልበት ሂደት ታመራለች። በምን የፖለቲካ አውታር እንደምትዘወር አይታወቅም። በሥልጣን ላይ የሚታየው ቡድን ወሳኝነቱ ተአማኒነት እንዳለው፤ ትዕዛዙ ተፈፃሚነት እንደሚኖረው፤ ማንስ እንደሚያከበረውና ደንታ እንደሚሰጠው በግልጽ ተለይቶ ከማይታይበት ደረጃ እየተደረሰ ነው።

2ኛ. ሠላምና መረጋጋጥ እየጠፋ፤ ሥርዓት አልበኝነት እየተስፋፋ፤ ህግና ደንብ አስከባሪ ኃይል እየተዳከመ የሚሄድበት አጋጣሚ መምጣቱ ኅብረተሰቡን በስጋት ላይ ሊጥለው የሚችል ሁኔታ ለመፍጠር የሚፈልጉ ኃይላት ሊበረከቱ የሚችሉበት አጋጣሚ ሊፈጠርላቸው ስለሚችል፤ ሁከቱንና ስጋቱን ለማባባስ ተግተው የሚሰሩበት ምቹ ሁኔታ ሊመቻችላቸው የሚችል አጋጣሚ አለ። ወይም በመምጣት ላይ ነው። ይኸ ሁኔታ እንዲመጣ፤ ወያኔ በህቡዕና በግልፅ እየሰራ ይገኛል።

3ኛ. ሀገሪቱ ከአደጋ ላይ ወደቀች፤ ብጥብና ረብሻ፣ ዝርፊያና ግድያ ተጀምሯል፤ ሀገር መፍረሷ አይቀርም፤ ስለዚህ ያ ከመከሰቱ አስቀድመን ሀገር ማዳን አለበን በሚል ማጠየቂያ፤ የወታደር መፈንቅለ አገዛዝ ተደርጎ፤ የአምባገንኖች መቀያየር ይደረጋል። ይህ ሁኔታ ደግሞ በተለያዩ የአፍሪካ ሀገራት ያሉ ወታደራዊ መፈንቅለ አገዛዞች ፈጽመውታል። የደርግ አገዛዝም የመፈንቅለ መንግሥት ውጤት ነበር። በአሁኑ ወቅት ደግሞ ወታደሩ ወደ ሥልጣን ላይ መጣ ማለት ወያኔ ሌላ ጥብቆ ለብሶ፤ ወደ ሥልጣን ተመልሶ መምጣት ማለት ነው። ምክንያቱም የትግራይ ተወላጆች የመከላከያና የፀጥታ መዋቅሮቹን ሁሉ ተቆጣጥረው ይዘውታልና ! የደኅንነቱና የስለላው መዋቅሮች አሁንም ገና ጨርሰው አልፈረሱም። ዛሬም አፋኞቹና ገዳዮቹ የወያኔ አባላትና ደጋፊዎች በዚያ አመለካከት የተቃኙት ናቸው። ወያኔና ቡችሎቹ ጨርሰው እስኪያከትሙ ድረስ ይህንን ኩነት አሌ ብሎ መፈጠም፣ መደምደም አይቻልም።

እነኝህን ሦስት ምናልባታዊ ግምቶች (ሲናሪዮ) በሀገራችን ፖለቲካ አየር ላይ እንዲንሳፈፉ የሆኑት ያለ ምክንያት አይደለም። በሥልጣን ላይ ያለው አገዛዝ ፤ ለዘለቄታ መፍትሄ ፍለጋው የህዝቡን ሙሉ ተሳትፎ በመገደቡና ተሳትፎው እንዲጠብ በመደረጉ ምክንያት ነው። ይህ ሁኔታ ለሥርዓት አልበኝነት አሞች ምክንያትን ፈጠረ። ለመሰለቻቸትና ተስፋ ለመቁረጥ ምክንያት እየሆነ በመምጣት ላይ ነው። የረዥም ርቀት አመለካከትን አንግቦ፤ ስትራተጂያዊ ዕቅድና ፖሊሲ በመንደፍ፤ ሀገርንና ሕዝብን ወደ ላቀ ደረጃ የሚያሸጋገር ሥርዓተ- መንግሥት ገና አልተመሰረተም። ያ ሥርዓተ መንግሥት ደግሞ፤ በሆያ ሆዬና በግርግር አይመጣም። በየአጋጣሚዎቹ፤ የማር ቅብ መፈክሮችን ማሰማት፤ ለሀገሪቱ ስር ለሰደዱ ችግሮች ማስወገጃ የሚሆን፤ ተመጣጣኝ መፍትሄ ሊያስገኝ አይችልም። የተደመር፤ ተደማመር ዐዋጅ፤ ያስገኘው ተፀምር እንደሌለ ይኸው እየታየ ነው። እንደመር ብለው ተጣድፈው የሄዱት ሁሉ ይኸው በመቅበዝበዝ ላይ ወይም ግራ ተጋብተው በመንሳፈፍ ላይ ናቸው።

ከተጫነበት የግፍ አገዛዝ ተላቅቆ አሁን ባገኘው አንፃራዊ የለውጥ እንቅስቃሴ፤ ደስተኛ መስሎ ቢታይም፤ ሕዝቡን በውቂው-ደብልቂው ስሜት ከማስተናገድ ይልቅ፤ በሰከነ ሁኔታ ወደ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት የሚያመራ አቅጣጫ ማሳየት በተገባ ነበር። ያ ግን እየሆነ አይደለም። በአሮጌ ስልቻ፤ አዲስ ማር ማስቀመጥና፤ በአረጀ በአፈጀ የወያኔ ዘረኛ ሥርዓት ላይ አዲስ ለውጥ ማስተናገድ ውጤታቸው አንድ ነው። ማሩም ይፈሣል ፤ ለውጡም ይኮላሻል። ትርፉ ኪሣራ ነው።

አዲሱን ህዝባዊ ለውጥ ባግባቡ ለማስተናገድ፤ ተገቢና ተስማሚ ተቋማት መትከል አማራጭ አይኖረውም። ሕዝባዊና ዴሞክራሲያዊ ተቋማት አስፈላጊነታቸው፤ ለሽግግር ውቅት ብቻ ሳይሆን፤ በዘለቄታ መልኩ፤ ለሀገር ጥቅም የሚሰጡት አግልግሎት ዘመንና ትውልድ ተሻጋሪ ይሆናል። ሕዝባዊ ተቋማት ሲባል፤ የፖለቲካ ድርጅቶችንም ሆነ የተለያዩ ዐላማዎችን ለማራመጃና ጥቅማ-ጥቅሞችን ማስፈፀሚያ ተቋሞችን ሳይሆን፤ ለጠቅላላው ሀገሪቷና ለዜጎቿ ዘለዓለማዊ ጥቅም ለመስጠት የሚቋቋሙ ሕዝባዊና ዴሞክራሲያዊ ተቋማትን መመስረት ማለት ነው። ተፈራራቂ አምባገነኖች፤ ለሥልጣናቸው መገልገያ የሚሆኑ ሠነዶቻቸውን፤ እንደ የሀገሪቱ "ሕግ መንግሥት" አስመስለው በማስፍን፤ ሕዝብ ሲጨቁኑበት ቆይተዋል። ወያኔም በበኩሉ፤ የሕወሃትን ድርጅታዊ ሠነድ እንደ ሕገመንግሥት አስቆጥሮ በመጫን ቀልዷል።

ከሁሉ አስቀድሞ ፤ ነፃና ሕዝባዊ የሆኑ ዴሞክራሲያዊ ተቋማት መገንባት፤ የወደፊቱን፤ ዴሞክራሲያዊ ሕገ መንግሥት ለማሰናዳት እንደ ድልዳል ሆነው ያገለግላሉ። በሽግግር ወቅት፤ ነፃ ተቋማትን መመስረት ወሳኝነቱ፤ ከዚህ አመለካከት አኳያ እንደሆነ አረዳድ መኖር አለበት።

የአገዛዝ ሥልጣን ለመጨበጥ ብቻ ታስበው የተመሰረቱ ተቋማት ሁሉ፤ እስከ ዛሬ ድረስ፤ ለአምባገነኖች የመጨቆኛ መሣሪያ በመሆን ፤ ይኸው እስካሁን በቀጣይነት፤ ከሕዝብ ጫንቃ አልወረዱም። ከሕዝብ መጨቆኛ አገልጋይነት ሊላቀቁ የሚችሉ፤ ነፃ ተቋማት ማየትን በጉጉት የሚጠብቀው የኢትዮጵያ ሕዝብ፤ ከተፈራራቂ አምባገነኖች አገዛዝ ለመላቀቅ ባለው ፅኑ ፋላጎት ነው። በአንፃሩ ደግሞ፤ ሕዝባዊና ዴሞክራሲያዊ የሆኑ፤ ነፃ ተቋማት ሕዝብ እንዲኖረው፤ አምባገነኖች አይፈልጉም። በነኝህ ሁለት ተፃራሪ ተቃርኖ ምክንያት፤ ባንድ ሀገር ውስጥ፤ አንዱ እየወደደው፤ ሌላው ግን የሚጠላውና የሚፈራው ነፃ ተቋም ለመመስረት ከቶ አይቻልም።

ይህንን መሠረታዊ ተቃርኖ ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ማስወገድ የሚቻለው፤ ሀገራችን፤ ዴሞራሲያዊ ሥርዓት ለመመስረት የቻለች ስትሆን ብቻ ነው። የደሞክራሲያዊ ሥርዓት መመስረት ጥያቄ፤ ያለመታከት ተደጋግሞ የሚነሳውም በዚህ ምክንያት ነው። እስካሁን ጥያቄው አልተመለሰም። ጥያቄ አቅራቢ እንጅ መልስ ሰጭ የለም። ሊኖርም ይችልም። ምክንያቱም ዴሞክራሲ፣ ነፃነትና መብት፣ እንዲሁም ፍትኅ- ርትዕ በሰጭና ተቀባይ፤ በችሮታና በአዘኔታ፤ የሚገኙ ባለመሆናቸው ነው። የሰው ልጅ ሰብዓዊ ፍጡር በመሆኑ ብቻ፤ የማይገፈፍ- የማይገሰስ- የማይነጠቅ- የማይለመንና የማይመፀወት ስጦታዎች አሉት። እነሱን ከተነጠቀ፤ በህጋዊም ሆነ ኢህጋዊ መንገድ መልሶ የማግኘት መብቱን ማስከበር አለበት። ለኢትዮጵያ ሕዝብ ይህንን መናገር ድፍረት ይሆናል ፤ በህይወቱ ኑሮ አይቶታልና - ምጥ ለናቷ ማስተማር ስለሚሆን !

የተለያየ ለምድና ማቅ እየለበሱ በመቅረብ፤ የኢትዮጵያ ተፈራራቂ አምባገነን ገዥዎች፤ የሕዝቡን የዴሞክራሲ ጥያቄ ለራሳቸው ሥልጣን መቆናጠጫ ተጠቅመውበታል፡፡ ከታንዛንያ ሶሻሊዝም፤ ወደ ኢትዮጵያ ሶሻሊዝም፤ ያ ሳይሆን ሲቀር ደግሞ፤ ወደ ቻይና በማቅናት ከፏከቱ በኋላ ለፈረሰው የትላንቱ ፤ ሶቬየት ኅብረት ተንበርክከው ሀገራችን የነርሱ ጥገኛ እስክትሆን ድረስ ማንነቷን አደብዝዘውት ቆዩ። ወያኔ በበኩሉ፤ የአልቤንያ ሶሻሊዝም ሲያቀነቅን ከርሞ፤ በአንድ ጠፍ ጨረቃ ተፈናጥሮ ለምዕራቡ ጎራ የሚያበቃውን ለምድ ለብሶ የሀገራችንን ሉአላዊነት አሳልፎ ሰጠ። የዴሞክራሲን ነባቢት በማቀንቀኑ ብቻ፤ አዲሶቹ የበላይ ጠባቂዎቹን ልብ የበላ በመምሰል፤ ተንበረከከላቸው። እነርሱም ፤ የኢትዮጵያን ሕዝብ የዴሞክራሲ ጥያቄ አልዘነጋነውም በሚል ዕሳቤ፤ "ዴሞክራሲ ከሌለ ርዳታ የለም !" የሚል ዲፕሎማሲያዊ ሽንገላን ተጠቅመው፤ የኢትዮጵያን ሕዝብ የዴሞክራሲ ጥያቄ ፤ የአፍዝዝ አደንዝዝ ምትኃት ለቀቁበት። የዚህ ሂደት የመጨረሻው ውጤት፤ ሀገራችንን ለሃያ ሰባት ዓመታት፤ የዘረኛ አገዛዝ ሰለባ አድርጓት ከረመ።

ጭቆና እስከቀጠለ ድረስ፤ ሕዝባዊ ዐመጽና አልገዛም ባይነት አይቀሬ በመሆናቸው፤ ይኸው ዛሬም በሕዝቡ ዐመፅ ምክንያት ሀገራችን በለውጥ ማዕበል ውስጥ ትገኛለች። የለውጡ አቦል የሕዝቡን ቀልብ የሳበው ፤ የወያኔ አገዛዝ እየተዳከመ በመምጣቱ ከዚያ አስከፊ ዘረኛ ሥርዓት የተላቀቀ መስሎት ነበር። በመሆኑም ለውጡን ማን ይምራው? ወዴትስ አቅጣጫ እየሄደ ነው? የለውጡ ደጋፊዎች አሰላለፍ ምን ይመስላል? ለውጡን የሚቃወሙ እነማን ናቸው ? ብርታትና ጥንካሪያቸውስ ምን ያኅል ነው? እና የመሳሰሉት ጥያቄዎች በአግባቡ አልተተኮረባቸውም ነበር። በዚህ ምክንያት፤ የሕዝቡ መራራ ትግል ያመጣውን ለውጥ፤ የገዥው አካል የሆነ ክፍል ሊቆጣጠረው ቻለ። ይህ ሊሆን የቻለው ደግሞ አስቀድሞ የተደራጀና የበቃ-የነቃ የተባበረ- ተቃዋሚ ኃይል ባለመኖሩ ነው። ይህ በሀገራችን ጸሐይ የሞቀው ዕውነታ ነው።
በቅርቡ የኢትዮጵያ ሕዝብ የትግል ታሪክ ተደጋግሞ እንደተከሰተው፤ ጨቋኝ አገዛዝን ታግሎ መጣል እንጅ፤ በምን ሥርዓት እንደሚተካ አይታሰብበትም ነበር። በዚህ ምክንያት፤ ከአሮጌ አምባገነን አገዛዝ፤ ወደ ሌላ ትኩስ አምባገነን አገዛዝ ከመውደቅ የተሻለ ዕድል አልነበረም። አድሞ መጣልና ማፍረስ እንጅ ፤ ተባብሮ አዲስ ሥርዓት መመስረትና መገንባት፤ የፖለቲካ ባኅላችን ሊሆን አልተቻለውም። የወቅቱ ሁኔታም የዚያ ድክመት ነፀብራቅ ነው። እየተወያዩ መለያየትን እንጅ፤ እየተደማመጡ ሲሆን የመዋሃድ ካልሆነ የመተባበርና

አብሮ የመሥራት የፖለቲካ ባኅል ሳይሆን ኖሯል። ይኽንን በሚገባ የተገነዘቡ የሥልጣን ጥመኞች ሁሉ፤ የፖለቲካውን ምኅዳር በሙሉ ጠቅልሎ በመያዝ አምባገነን አገዛዝ ለመመስረት አይቸገሩም። ሕዝብ በላቡና በደሙ የከፈለውን መሥዋዕት፤ ነፍጥ ያነገቡ ኃይሎች ለራሳቸው ሥልጣን መቆናጠጫ ሲያደርጉት ኖረዋል።

ዛሬ በመካሄድ ላይ ያለውን የለውጥ እንቅስቃሴ ያስገኘው፤ የሕዝብ መራራ ትግል መሆኑ እየታወቀ፤ አስቀድሞ የተዘጋጀ ሕዝብዊ ኃይል ባለመኖሩ ምክንያት ብቻ ፤ ከገዥው ክፍል ውስጥ አድፍጦ ሲጠባበቅ የነበር አንድ ቡድን፤ አጋጣሚውን ተጠቅሞ የለውጡን አግማስ ተሻምቶ የተንገዳገደውን ሥልጣኑን እንደምንም አውሸልሽሎ አገዛዙ ዕድሜውን ለማራዘም ዕድል አገኘ። ሲገለገልባቸው የቆየውን፤ መንግሥታዊ ተቋማትና ሌሎች የመጨቆኛ መሣሪያዎችን እየተጠቀመ ያለ በመሆኑ፤ ሕዝቡ ከስጋት ፈጽሞ ነፃ ሊሆን የሚችለበት ሁኔታ አልታመቻቸለትም። የገዥው ቡድን፤ አንዳንድ ጥገናዊ መሰል ብወዛዎችን እያሳየ፤ ሕዝባዊውን የመሠረታዊ ለውጥ ጥያቄ ማኮላሸቱን ቀጥሎበታል። የሕዝቡ የሥርዓት ለውጥ ጥያቄ በማር-ቅብ ቃላት እየተሸነጋገሉ ተድበስብሰው እንዲቀሩ በመደረግ ላይ ናቸው።

በድቅድቅ ጨለማ ስር ወድቆ በመረር አገዛዝ ሲማቅቅ የነበረ ሕዝብ፤ ሊሰማ የሚፈልገውን ከሰማ፤ ዕፎይታን ያገኛል ከሚል ዕሳቤ በመነሳት፤ ሕዝበኛ ንግግር በማሰማት፤ የሕዝቡን ዴሞክራሲያዊ ጥያቄ ማፈን የሚቻል አይደለም። አሁን ያለው የገዥ ቡድን፤ በዚህ የፖለቲካ ፈሊጥ ለማወናበድ ይሞክራል። የዚህ ዓይነት ፖለቲካ ሡንጠርዥ ጨዋታ፤ ምናልባት ከሃምሳ ዐመታት በፊት ለነበረው የሀገራችን ኅብረተሰብ ሠርቶ ይሆናል። በሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን ለሚኖረው የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን ከቶ ሊሠራ አይችልም።

በአሁኑ ወቅት ወደ 108 ሚሊዮን ከሚሆነው የሕዝባችን ቁጥር ውስጥ ስድሳ አምስት ከመቶ (65%) የሚሆነው ወጣት ትውልድ እንደሆነ ተገምቷል። የዚህ የኅብረተሰብ ክፍል አመለካከት፣ ፍላጎት፣ ምኞት፣ ነቃተ- ኅሊና፣ ሥነልቡና፣ ቋንቋና የአገላለፅ ዘየ፣ የኃሳብ ነፃነትና የሁኔታዎች ግንዛቤና አረዳድ ሁሉ አዲሱ ክፍለ ዘመን ከሚያስተዋውቀው ሳይንስና ቴክኒዮሎጂ ጋር የተያያዘ ነው። በመሆኑም ለዚህ የኅብረተሰብ ክፍል የሚስማማ የፖለቲካ፣ የምጣኔ ሀብት፣ ማኅበራዊና ባኅላዊ ዕሴት፣ የታሪክና ዕምነት መስተጋብርን የሚያስተናግድ የፖለቲካ ሥርዓት መዘርጋት በይደር ሊተላለፍ የሚችል ጉዳይ አይደለም። ይህን ሁሉ ግምት ውስጥ በማስገባት ነው ፤ ዛሬ የኢትዮጵያ ሕዝብ ለሥርዓት ለውጥ የሚታገለው፡፡

የሥርዓት ለውጥ ጥያቄን፤ የባለሥልጣናት የቦታ ልውውጥና ሹም-ሽር አይመልሰውም። በዘውግ ላይ የተገነባ ዘረኛ ሥርዓትን የመሠረተው የወያኔ ሕገ-መንግሥት መፍረስ የመጀመሪያው እርምጃ መሆኑን መላው ሕዝብ ያምናል። ፌደራላዊ አስተዳደር አስፈላጊ በሆነበት ለነዋሪዎች ምቹና ተገቢ፣ ተስማሚ፣ ተፈላጊና ተመራጭ የሆነ የሀገር አስተዳደር ሥርዓት- መንግሥት ነው - በተለይም እንደኢትዮጵያ ሰፊና የበርካታ ቋንቋዎችና ባኅል ስብጥር በሆነችበት ሁኔታ። የኢትዮጵያን ሕዝብ በቋንቋ ክልል ወስኖ መግዛት ግን ፤ ሰብዕናውን ብቻ ሳይሆን ክብሩን፤ እንደሀገር ታላቅ ህዝብነቱን፣ ኩራቱን፣ ታሪክና ባኅሉን መፈታተንም ጭምር ሆኗል። ይህ ዘውጋዊ ሥርዓት፤ በሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን፤ በየትኛውም የዐለም ክፍል የሚኖር ሕዝብ የሚኮንነው ነው። ሕዝባችን ጸጋዎቹ የሆኑትን ልዩ ልዩ ባህላቱ ቋንቋዎቹ፣ በዕኩልነት የሀገሩ አንድነትና ሉዓላዊነት በተከበረባት ኢትዮጵያ ማየት፤ ዕውን ማረግ አጥብቆ ይፈልጋል። በምንም ዓይነት ያንዱን ቋንቋ፣ ሆነ ባህል አሳንሳ የምታይ ኢትዮጵያን ዳግም ማየት አይፈልግም። በመሆኑም የሕዝባችን ቀዳማይ ጥያቄ የሥርዓት ለውጥ ስለሆነ፤ የኢሕአዴግን አገዛዝ እስከነኮተቱ ሊያፍርሰው ቆርጦ ተነስቷል።

የሕዝቡ መራራ ትግል፤ ይህን ለውጥ አስገኝቷል። ለውጡ አዲስ የተስፋ ምዕራፍ እንደከፈተላቸው ዜጎች ሁሉ ያምናሉ። ተስፋቸው ዕውን እንዲሆን ደግሞ ተጨባጭ ውጤትን ማየት ይፈልጋሉ። የሚፈልጉትን የሥርዓት ለውጥ እስኪያገኙ ድረስ ትግላቸውን ይቀጥላሉ። አለባብሰው የሚያርሱ ሁሉ ግን ወደ ዐረም ይመለሳሉ እንጅ፤ ውጤት አያስመዘግቡም። ኢሕአፓ ግን አረሙን እየነቀለ፤ ይታገላል - ከዐረም በፀዳው ማሣ ዴሞክራሲዊ ሥርዓት እስከሚገነባ !

የኢትዮጵያ ሕዝብ ያቸንፋል !